# አንድነትና መኢአድ በመጪው ምርጫ ያላቸው ስፍራ

ክፍል ሁለት

ኢብሳ ነመራ

12-24-14

በዚሁ ርእስ በቀረበ ክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ ከመጪው ሃገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መኢአድና አንድነት በውስጣቸው ያለውን አለመግባባት እንዲያጠሩ ያቀረበላቸውን ማሳሰቢያ መነሻ በማድረግ የመኢአድን የውስጥ ችግር የፓርቲውን አባላትና አመራሮች በዋቢነት ጠቅሰን ተመልክተናል። በዚህ ፅሁፍ ደግሞ የአንድነትን የአመራር ውዝግብ እንመለከታለን።

አንድነትም ቢሆን ከአንድ ወር በፊት ከመኢአድ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የአመራር ውዝግብ ውስጥ ገብቶእነደነበረ ይታወሳል። 2007 ዓ/ም በገባ ማግስት አምስት የአንድነት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በድንገት ከሃላፊነታቸው የመነሳት ጥያቄ አቀረቡ። በወቅቱ የፓርቲው ሊቀመንበር የነበሩት ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላቱን ከስራ የመነሳት ጥያቄ ተቀበለው አሰናበቷቸው። በፍቃዳቸው ስራቸውን በለቀቁተ የስራ አስፈፃሚ ኮሞቴ አባላት ምትክም ሌሎች ሰየሙ። ሁኔታው ግን በዚህ አላበቃም።

ይህ ሆኖ ብዙም ሳይቆይ የፓርቲው ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ከሃላፊነታቸው የመነሳት ጥያቄ ማቅረባቸው ተሰማ። ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ከአቶ ግርማ ሰይፉ ጋር ጋር ፓርቲውን ለመምራት ተፎካክረው እጅግ በከፍተኛ አብላጫ ድምፅ አሸንፈው ፓርቲውን የመምራት ስልጣን ተረከበው ገና ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው ከሃላፊነታቸው የመነሳት ጥያቄ ማቅረባቸው በፓርቲው አባላት ዘንድ ግራ መጋባትና ድንጋጤ ፈጥሮ ነበር። እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ባለውና ኢ/ር ግዛቸውን በመረጠው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ዘንድ አሳዛኝ ሁኔታ ፈጥሮም ነበር።

ኢ/ር ግዛቸው ከፓርቲ አመራርነት ለመነሳት ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ ለዚህ ውሳኔ ያበቃቸውን ምክንያት ይፋ አደረጉ። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በይፋ በሰጡት መግለጫ "ዋናው

የለቀኩበት ምክንያቴ በአጠቃላይ መልኩ ከውስጥ እና ከውጪ ሀገር በአንድነት ፓርቲ ላይ በተደረገ ኢ-ተቋማዊ፣ ኢ-ደንባዊ እና ቡድናዊ ተፅዕኖ ምክንያት ነው። የአንድነትን ሥራ ከተቋም፣ ከደንብ የማስወጣት ሥራ ስላለ ነው። ይህንን ነገር በሁለት ከፍዬዋለሁ። በውጪ ሀገር እና በሀገር ውስጥ በተደረገ ቡድናዊ ተፅዕኖ በሚል። በውጪ ሀገር ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮያዊያን የምንላቸው ከ10 እስከ 20ሺ ኪሎ ሜትር ርቀው ያሉ ዲያስፖራዎች ከፍተኛ ክብር የምንሰጣቸው ናቸው። ሦስትም ሆነ ሃያ ዓመታት በውጪ ሀገር ተቀምጠው ሀገራቸውን አልረሱም። በፖለቲካው አካባቢም የተሻለ ለውጥ እንዲኖር አጠቃላይ ዲያስፖራው ያለውን አስተዋፅኦ በበጎ መልኩ ነው የማየው። ለዚህም በግሌ ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት አለኝ። ነገር ግን አጠቃላይ መልኩ ጥሩ ሆኖ በአጋጣሚ በአንዳንድ መሪነት የሚቀመጡ ሰዎች ያለውን በጎ ነገር ለመጥፎ ሥራ ይጠቀሙበታል። የአንድነት የድጋፍ ሰጪ ማኅበራት በውጪ ሀገር አሉ፤ እነሱ በእኔ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርገዋል። ኢ-ተቋማዊ፣ ኢ-ደንባዊ በሆነ መንገድ።

አንድነትን እንደ ኤጀንት የመጠቀም ፍላጎት አላቸው። በገንዘብ ይረዱናል፣ በዚያ ምክንያት የማዘዝ፣ የአንጋሽነት ሚና ለመጫወት ይሞክራሉ፤ ይህንን ደግሞ እኔ አልቀበልም። እነሱ የፓርቲው ደጋፊ ናቸው እንጂ የወሳኝነት ቦታውን ይዘው፣ ‘ግዛቸው ይውጣ፣ እገሌ ይምጣ’ ሊሉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። እናም በየሚዲያውና ማኅበራዊ ድረገጾች ከፍተኛ ዘመቻ ነው ያካሄዱት። ይህም የሆነበት ምክንያት በእነሱ ትዕዛዝ ባለመመራቴ ነው። እኔ ደግሞ እስካለሁ ድረስ አንድነት የራሱ ተቋም፣ ብሔራዊ ም/ቤት አለ፣ ጠቅላላ ጉባዔ አለ፣ ፓርቲውን የሚያንቀሳቅሰው በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ነው። እነሱ ደጋፊዎች ናቸው፣ እንደ ኢትዮጵያዊ ድምፃቸው ማሰማት፣ ሃሳባቸውን መግለጽ ይችላሉ። ግን አሠራሩ መዋቅራዊ መሆን አለበት። ግዛቸውን ካልፈለጉት እኔን የሚያወርደኝ ጠቅላላ ጉባዔ እና ብሔራዊ ምክር ቤቱ ነው። ስለዚህ ለእሱ ደብዳቤ መፃፍ ይችላሉ። በራሳችን ድረገጽ ላይ ‘ግዛቸው ይውረድ፣ ፒቲሽን እንፈራረማለን’ የሚለው እጅግ አሳፋሪና ኢ-ተቋማዊ፣ ኢ-ደንባዊ፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ነው። ይህ ሁኔታ ከፍተኛ ልዩነት ፈጥሯል። በዚህ ምክንያት የገንዘብ ማዕቀብ አድርገዋል። የሚያሳዝነው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲ የውጪ ሀገር ጥገኛ ነው። የሪሶርስ፣ የገንዘብ ጥገኛ ነው። ይሄ የሚያሳፍር ነው። በእኛም በኩል ይሄ ነገር እንደ ድክመት መውሰድ አለብን። ይህንን የገንዘብ ግንኙነታችንን መሠረት በማድረግ እኛን ማዘዝ ይፈልጋሉ። እኔ ደግሞ ዓላማ

*አለ፣ መርህ አለ፣ ደንብ አለ፣ ተቋም አለ፤ የአንድነት ኃይል ያለው አዲስ አበባ ነው። ከውጪ የሚመጣ ኃይል አይነቀንቀውም የሚል ጽኑ አቋም አለኝ።"* ብለው ነበር። ይህ ሁኔታ በፓርቲው አመራርና አባላት ዘንድ ሰፊ አለመግባባት ፈጥሯል።

ያም ሆነ ይህ ፓርቲው በኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ምትክ አዲስ ሊቀመነበር አስመረጠ። አዲሱ ሊቀመንበረ የተመረጡት በጠቅላላ ጉባኤ ሳይሆን በበሄራዊ ምክር ቤቱ ነው። በዚህም ከስራ ተሰናብተው ከነበሩት የአንድነት ስራ አስፈፃሚ ኮሞቴ አባላት መሃከል አንዱ የሆኑት አቶ በላይ ፍቃዱ የፓርቲው ሊቀመነበረ ሆነው ተሰየሙ። የሌሎች አመራሮችም ለውጥ ተካሄደ። ይህ የአመራር ለውጥ "የፓርቲውን ህገደንብ የተከተለ አይደለም" የሚሉ ወገኖች ተነሱ። ብሄራዊ ምርጫ ቦርድም በህገደንቡ መሰረት የተካሄደ መሆኑን ለማረጋገጥ ለፓርቲው ጥያቄ አቀረበ።

በዚህ ዙሪያ በአዲሱ የስልጣን ሹም ሽር ምክትል ሊቀመነበር ሆነው የተመረጡት አቶ ግርማ ሰይፉ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ ፣ *" 'በደንባችን መሠረት ጠቅላላ ጉባኤ በሌለበት ምክር ቤቱ የጠቅላላ ጉባኤውን ሥራዎች ወክሎ ይሰራል' ይላል። ይህ ማለት የድርጅቱን ፕሮግራም እና ደንብን ማሻሻል አይጨምርም። ከጠቅላላ ጉባኤ ስራዎች መካከል አንዱ የፓርቲውን ሊቀመንበር መሰየም ነው። ጠቅላላ ጉባኤው የሚጠራው በሶስት ዓመት አንዴ ነው። ስለዚህም ምክር ቤቱ የተፈጠረውን የኃላፊነት ክፍተት ጠቅላላ ጉባኤው በሰጠው ውክልና መሰረት ሊቀመንበር ለመምረጥ ችሏል። ይህን ሂደት በምንም መልኩ ሕገወጥ ሊያስብለው የሚችል መሰረት የለም። ስለዚህም ሊቀመንበሩ በደንቡ መሰረት የተመረጠ ነው። በነገራችን ላይ ይህን ሂደት የሚቃወሙ ሰዎች በዚህ ሂደት ለምርጫ ቀርበው ባገኙት አነስተኛ ድምጽ የተሸነፉ ናቸው። ሂደቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ቢኖረው፣ እነዚህ ውንጀላ የሚያቀርቡ ወገኖች ለሊቀመንበርነት መወዳደር ሳይሆን አካሄዱን በመቃወም በግልፅ መሟገት ነበረባቸው። እነሱ ግን፣ ምክር ቤቱ ውሳኔ ካሳለፈ በኋላ ለአብላጫው ድምጽ መገዛት ሲገባቸው ወደ ውንጀላ አመሩ። ተገቢነት የሌለው ተግባር ላይም ተሰማሩ። ስለዚህም መከራከሪያቸው ውሃ የሚቋጥር አይደለም።"* ሲሉ ተናገሩ።

ሌሎች የፓርቲው አመራሮችም አጠቃላይ የስልጣን ሹም ሽር ሂደቱ ላይ ከረር ያለ ተቃውሞ አሰምተዋል። ከእነዚህ መሃከል የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የነበሩት ኢ/ር ዘለቀ ረዲ የገኙበታል።

ኢ/ር ረዲ በጉዳዩ ዙሪያ በሰጡት አስተያየት “አምስቱ ሥራ አስፈፃሚዎች በፈቃዳችን ከኃላፊነት ለቀናል ያሉበት አግባብ ሕገወጥ ነበር። ምክንያቱም በቡድን ተደራጅተው በአንድ ቀላጤ ወረቀት ‘ለቀናል’ ብለው ነው ያስገቡት። በሚገርም ሁኔታ አንዱ ለሌላው ‘ስለ እንትና’ የሚል ፊርማ አቅርበው ነበር የለቀቁት። በወቅቱ ተቀዳሚ ሊቀመንበር ለነበሩት ለአቶ ተክሌ አሁን ሊቀመንበር ተብለው የተመረጡት አቶ በላይ ናቸው ስለ ብለው ለአቶ ተክሌ መልቀቅ ፊርማቸውን ያኖሩት። አንድ ሰው ለሌላ ሰው መፈረም የሚችለው ሕጋዊ ውክልና ሲኖረው ብቻ ነው። ከውክልና ውጪ የሚፈረም ፊርማ ሕገወጥ ነው።

ይህን ሕገወጥ ስራቸውን ፕሬዝደንቱ ለምክር ቤቱ በወቅቱ አሳውቀዋል። የተፈጸመውን ሕገወጥ ስራ ምክር ቤቱ መመልከት ነበረበት። ‘ምክር ቤቱ ለምን በቀጥታ ተቀበለው?’ ካልን ምላሹ የሚያሳየው፣ ከተቀዳሚ ሊቀመንበር እስከ ፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ድረስ በአድማ መልቀቃቸው ፓርቲውን በተቀናበረ ሴራ ለማሽመድመድ የሰሩት ስራ እንደነበር ነው። መልቀቅ መብት ቢሆንም ከአንድ ፓርቲ የለቀቀ አመራርም ሆነ ቡድን በእጁ ያሉ ንብረቶችን አስረክቦ መሄድ አለበት። በጣም የተሻለ ስብዕና ያለው ከሆነ መልቀቁን አስመልክቶ ቀደም ብሎ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ እስከሚለቅ ድረስ አዲስ አመራሮችን አለማምዶ አሰልጥኖ ተክቶ በክብር ይሄዳል። እነዚህ ግን በቡድን ተደራጅተው ከለቀቁ በኋላ ወደ ፖለቲካዊ ሴራ ውስጥ ነው የተነከሩት። በግልፅ የመታገል መብት እያላቸው ነው፣ የጓሮ በር የፈለጉት።

ይህ የተደራጀው የሥራ አስፈፃሚ ቡድን እና በምክር ቤቱ ያደራጃቸው አባላት ፍላጎት ኢንጅነር ግዛቸውን ለማውረድ የሚፈልጉ በመሆናቸው፣ በመልቀቃቸው ላይ መነሳት የነበረበት የህግ ጥያቄ ተድበስብሶ እንዲቀር ነበር የተደረገው። የተጠቀሙበት መንገድ በፍቃደኝነት ስለለቀቁ መቀበል እንጂ ውይይት አያስፈልግም የሚል አንደምታ ነበረው። ይህን ያደረጉት ደግሞ ለቀጣይ ፖለቲካዊ ሴራቸው እንዲያመቻቸው ነበር።

በቡድን እንዲለቁ የተደረጉት የመታገያ ምክንያት እንዲሆናቸው ነው። ለምሳሌ እነዚህ ሥራ አስፈፃሚዎች ከለቀቁ በኋላ አዲስ የተሰየመው ሥራ አስፈፃሚ ሳያውቅ መቀሌ ድረስ በመሄድ ከፓርቲው ፍላጎት ውጪ ያልተገባ ተግባር ፈጽመዋል። ይህን ያረጉት የፓርቲው ምክትል አፈጉባኤ አቶ ፀጋዬ አላምረው እና አቶ አስራት አብርሃ ከሥራ አስፈፃሚው

*እውቅና ውጪ መቀሌ አባላት ለማደራጀት ሄደዋል። ይህ የሚያሳይህ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለአዲሱ ሥራ አስፈፃሚ እውቅና አለመስጠት እና በቡድን ተደራጅቶ ከለቀቀው የሥራ አስፈፃሚ ቡድን ጋር ያላቸውን ፖለቲካዊ ሴራ በይፋ ያረጋገጡበት መንገድ ነው። ይህ ተልዕኮቸው ኢንጂነር ግዛቸውን ተቀባይነት በመንሳት እና በሕገወጥ መንገድ ፓርቲውን ለማሽመድመድ የነበራቸው ፍላጎት ማሳያ ነው።*

*ኢንጅነር ግዛቸውን በእነዚህ ኃይሎች ጥርስ ውስጥ ያስገባቸው ዋናው ጉዳይ፣ ከዲያስፖራ የሚሰበሰበው ገንዘብ በሕጋዊ የአንድነት የሂሳብ ቋት ውስጥ በቀጥታ እንዲገባ መጠየቃቸው ነው። ይህ የኢንጅነሩ አካሄድ ተቋማዊና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ስለሚያሰፍን፣ ፍርፋሪ የሚለቃቅመው አንጃ አደጋውን ቀድሞ የተረዳ በመሆኑ፣ ፓርቲውን በማዳን ስም ወደ ሕገወጥ አደረጃጀት  ተንቀሳቀሰ። የሚገርመው እንደጅራፍ እራሳቸው ገርፈው በማሕበራዊ ድረ ገጽ እራሳቸው እየጮሁ ይገኛሉ። ቁጭ ብለው መከራከር አይችሉም። ጥያቄያቸው የዳቦ የደመወዝ ጥያቄ በመሆኑ ነው።"* ነበር ያሉት።

እነዚህ ከላይ የተገለፁ ሁኔታዎች በመኢአደና በአንድነት ፓርቲዎች ውስጥ የአመራ አለመግባባት መኖሩን የሚያሳዩ፣ በመንግስት ወይም በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሳይሆን በራሳቸው በፓርቲዎቹ አመራሮች ምስክርነቶች ናቸው። ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ  ማለትም ለአንድነት ፓርቲ በውስጡ ያለውን የአመራር አለመግባባት ፈትቶ እንዲቀረብ ቀን ቆርጡ ያቀረበለት ጥያቄ መነሻ ይህ በፓርቲው  አመራሮች የተመሰከረለት ውስጣዊ ችግር ነው።

ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎቸ ወይም የአመራሮቻቸውና የአባላቶቻቸው ጉዳይ አይደለም። ምርጫ በዋናነት የህዝብ ጉዳይ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎቸ በፈቀዱት አመለካከት ላይ የመደራጀት ሕገተመንግስታዊ መብት ቢኖራቸውም "ለፖለቲካ ስልጣን ምረጡን" ብለው ወደ ህዝብ ሲቀርቡ በአደረጃጀትና በአመራር ህጋዊ ስርአትን የተከተሉና "ለህዝቡ እናደርጋለን" የሚሉትን የመፈፀም ድርጅታዊ አሰራር ያላቸው መሆኑ መረጋገጥ አለበት። በመሆኑም በምርጫ ላይ ለመወዳደር የሚቀረቡ ፓርቲዎች ድርጅታዊ አወቃቀር፣ አመራርና አቋም በፓርቲዎቹ ህገደንብ፣ በህገመንግስቱንና ሌሎች የሃገሪቱን ህግ መሰረት በማደረግ በተዘጋጀ የፓርቲዎቹ ህገደንብ፣ እንዲሁም ሌሎች ህጎችን የተከተለ፣ ከውስጣዊ ውዝግብና ሹክቻ የፀዳና በህዝብ በግልፅ የሚታወቅና ተአማኒ የሆነ ሊሆን ይገባዋል።

እናም መኢአድና አንድነት የውስጥ ችግራቸውን ፈትተው እንዲመጡ በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረበላቸው ጥያቄ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተአማኒ ምርጫ እንዲካሄድ በህገመንግስት የተሰጠውን ሃላፊነት የመወጣት አካል ነው። ህጋዊና ተገቢ ጥያቄም ነው።

ይሁን እንጂ በተለይ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ከምርጫ ቦርድ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በተሰጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ወደምርጫው መግባት የሚያስችለውን ምላሽ መስጠት ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ ጉዳዩን ወደተቃውሞ አጀንዳነት ሊቀይረው ሞክሯል። የሻአቢያ ተላላኪ የሆኑ በውጭ ሃገራት የሚገኙ ቡድኖች ልሳናት እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ ትርምስ ያለ አስመስለው በማውራት በውጭ የሚኖሩ የዋህ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን አደናግረው መተዳደሪያቸውን የሚሸቅሉ ጥገኞች የአንድነትን አጀንዳ ተቀበለው ሊያሟሙቁት መክረዋል።

አንድነት ምርጫ ቦርድ ላቀረበበት በፓርቲው ውስጥ ያለ የአመራር አለመግባባት ችግር ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያለውን ፈቃደኝነት ከመግለፅ ይልቅ “በምርጫ ቦርድ ደባ አንድነት አይደናገጥም” የሚል መፈክር ቢጤ ርዕስ ያለው መግለጫ አውጥቷል። በዚህ መግለጫ “. . . ፓርቲው 320 የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን በመጥራት የምርጫ ቦርድ ተወካይ በተገኙበት የተሳካና አንፀባራቂ ጉባኤ አካሂዷል። የጠቅላላ ጉባኤው ሰነድ ታህሳስ 10፣ 2007 ዓ/ም ለምርጫ ቦርድ ገቢ ተደርጓል” በሏል።

አንድነት ፓርቲ ይህን ማድረጉ እውነት ሊሆነን ይችላል። ምርጫ ቦርድም ለፓርቲው በላከው ደብዳቤ ይህን አረጋግጧል። ምርጫ ቦርድ አንድነት ታህሳስ 3 የጠቅላላ ጉባኤ አካሂዶ የጠቅላላ ጉባኤና የምልዐተ ጉባኤ አባላትን ቁጥር አካቶ ያዘጋጀው ሀገደንብ ቢደርሰውም የጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ስላልደረሰው ይህን እንዲያቀርቡለት ነው የጠየቀው። በዚህ ሪፖርት በፓርቲው ውስጥ ያለው የአመራር አለመግባባት በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ መረዳት ሰለሚችል ሊሆን ይችላል ሪፖረቱ ይቅረብልኝ ያለው። አንድነት “አንፀባራቂደማቅ ምንትስ ቅብጥርስ . . .” እያለ የሚያሞካሸውን ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርተ መላክ ለምን እንደከበደው ግን ለብዙዎች ግልፅ አይደለም።

ምርጫ ቦርድ ለአንድነት ፓርቲ ባቀረበው ጥያቄ ውስጥ ምንም ስውር ደባ የለም። ጥያቄው ግልፅ ነው። የቀረበውም በይፋ ነው። አንድነት ለቀረበለት ቀላል ጥያቄ ምላሽ በመስጠት ከውዝግብ የፀዳ ቁመና ይዞ ወደምርጫ ለመግባት ከመጣደፍ ይልቅ "የምርጫ ቦርድ ደባ ምንትስ" የሚል መሰረተ ቢስ ተቃውሞ በሻአቢያ ተላላኪዎች ልሳን መፎከር መምረጡ በአመራሩ ውስጥ ያለውን ችግር በአግባቡ መፍታት መቻሉን ጥያቄ ውስጥ ከቶታል።

አንድነት በተውገረገረ አደረጃጀትና በሚወዛገብ አመራር ያለበትን ውስጣዊ ችግር በባዶ ፉከራ አድበስብሶ ወደምርጫ መግባት ነው የፈለገው። ይህን ለምን እንደፈለገ ቀሰ ብለን የምናየው ይሆናል። አንድነት እውነት ምርጫው ላይ መሳተፍና በምርጫው የህዝብ ውክልና ማግኘት ብቻ ከሆነ የሚፈልገው ከነአስከፊ ውስጣዊ ችግሩ ወደምርጫው መግባት አያዋጣውም። በህዝብ ውክልና ቢሰጠው የህዝብን አደራ ከመወጣት ይልቅ እርስ በርስ ወደመወዛገብ ነው የሚያመራው። ይህ ደግሞ ለህዝብ ቆሜያለሁ ለሚል የፖለቲካ ፓርቲ የሚጠበቅ አይደለም።

አንድነት ከነችግሩ ወደምርጫ ለመግባት የሄደው፣ በዚህ ሁኔታ ምርጫው ውስጥ መግባት እንደማይችል ሲነገረው ደግሞ ሰሰሞኑን እንዳደረገው "ምርጫው ላይ እንዳልሳተፍ ተከለከልኩ" የሚል ውዥንብር በመንዛት ለህገወጥ የፖሎቲካ እንቅስቃሴ መግቢያ ሰበብ ፍለጋ ከሆነም ተሳስቷል። ይህ አካሄድ በውጭ ሃገር የሚንቀሳቀሱ ኢሳትንና ዘሃበሻን የመሳሰሉ የሻአቢያ ተላላኪዎች ዜና ከመሆን ያለፈ በህገወጥ መንገድ ፍላጎቱን ማሟላት እንደማይችለው ማወቅ ይገባዋል። አሁን እጅግ አብላጫው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ገዢውን ፓርቲ የማይደግፉ ጭምር ሰላማዊ ያልሆነ ህገወጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴና በዚህ መንገድ የሚመጣ የስልጣን ሽግግር የማይቻል እነደሆነ ይረዳል። እንደአጋጣሚ ቢሳካ እንኳን ሃገሪቱን ዳግም ሃገር ልትሆን በማትችልበት ሁኔታ የግጭትና የትርምስ አውድማ ከማድረግ ያለፈ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ወገን ተጠቃሚ ማድረግ እንደማይቻልም ይረዳል። በዚህ ረገድ ሕዝቡ ከፖለቲካ ፓርቲዎቹ አመራሮች ልቆ ሄዷል። በመሆኑም ጥቂት የሻአቢያ ጉዳይ አስፈፃሚዎች ካልሆኑ በስተቀር ህገወጥ አካሄዱን የሚቀበል የለም።

አንድነት "ምርጫ 97ን ተከትሎ ተቀስቅሶ የነበረው አይነት ሁከት ሊቀሰቀስ ይችላል፣ ይህም የስልጣን መንገድ ሊሆን ይችላል" ብሎ አሰቦ ከሆነም አሁን ያለውን ነባረዊ ሁኔታ

አያውቀውም ማለት ነው። ራሱ የ97ን ምርጫ ተከተሎ ተቀስቅሶ የነበረው ሁከት በሁለት ሶስት የሃገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ለዛውም ጥቂት ምንም የማያውቁ ስሜታዊ ወጣቶች ብቻ የተሳተፉበት ህዝባዊ መሰረት ያልነበረው መሆኑ ሳይዘነጋ አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ ምንም አይነት ሁከትም ሊነሳበት የማይችል ነው።